# MY SCHOOL DC
# መመሪያ

MY SCHOOL DC
የሕዝብ ት/ቤት ሎተሪ

## የ2025-26 የትምህርት ዘመን





info.myschooldc@dc.gov
202-888-6336 www.myschooldc.org


OSSE
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የትምህርት ቤትዎን ዝርዝር ያዘጋጁ

ይህን የቀመር ሉህ ተጠቀመው መማር የሚፈልጉባቸውን ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ያዘጋጁ። **School Finder** ን በመጠቀም ፍለጋዎን መጀመር ይችላሉ። አንድ ጊዜ እያንዳንዱን ትምህርት ቤት ካጠኑ በኋላ፣ በጣም በሚወዱት ቅደም ተከተል ይዘርዝሯቸው። በMy School DC ማመልከቻ ላይ እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ ማመልከት ይችላሉ፣ እና እነሱን በጣም በፈለጋችሁት ቅደም ተከተል ደረጃ መስጠት ያስፈልግዎታል።

| የትምህርት ቤት ስም | ክፍት የትምህርት ቤት ቀን | ማስታወሻዎች<br>ለእርስዎ እና ለልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ምንድን ነው? የትኞቹ ትምህርት ቤቶች ተስማሚ ናቸው? | ደረጃ |
|---|---|---|---|
| **ምሳሌ፡-**<br>ትምህርት ቤት ABC | *1/9/25*<br>(ምናባዊ ክፍለ ጊዜ) | ትምህርት ቤቱ በሳይንስ እና ሂሳብ ላይ ያተኩራል፣ ይህም ለልጄ ተስማሚ ነው፤ ነገር ግን ትምህርት ቤቱ የሚገኘው እኛ ከምንኖርበት ቦታ 3 ማይሎች ርቀት ላይ ነው (የትራንስፖርት አማራጮችን ማጥናት ያስፈልጋል) | *3* |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |



**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

ቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline በ (202) 888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።

# የMY SCHOOL DC አጠቃላይ እይታ

My School DC ለሁሉም በዲስትሪክቱ ውስጥ ለሚገኙ ከ PK3 –12ኛ ክፍል ለሚያገለግሉ ተሳታፊ የዲሲ የሕዝብ እና የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የተለመደ ማመልከቻ እና የሕዝብ ትምህርት ቤት ዕጣ ነው።

## የ2025-26 የትምህርት ዓመት የእጣ ቀነ ገደቦች:-

ፌብሩዋሪ 3:- ከ 9-12ኛ ክፍሎች | ማርች 3:- ከ PK3 – 8ኛ ክፍል

## ሶስት ደረጃዎች የ My School DC አሉ:-

1. **ትምህርት:-** ለእርስዎ እና ለልጅዎ በጣም ጠቃሚ የሆነውን ነገር ያስቡ፣ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች ዝርዝር ያዘጋጁ እና የትኛዎቹ ትምህርት ቤቶች ቅድሚያ ከሚሰጧቸው ነገሮች ጋር በተሻለ ሁኔታ እንደሚጣጣሙ ለመለየት የትምህርት ቤት አማራጮች ላይ ጥናት ያድርጉ።
2. ***ያመልክቱ*** የቤተሰብ አካውንት ለመፍጠር እና ማመልከቻዎን ለመጀመር ወደ **MySchoolDC.org/am** ይሂዱ፣ የትምህርት ቤት ምርጫዎን በጣም በፈለጋችሁት ቅደም ተከተል ደረጃ ይስጡ እና ማመልከቻዎን በማመልከቻው ቀነ-ገደቦች ያስገቡ።
3. ***ይመዝገቡ፣*** ልጅዎ ለመመዝገብ ፍቃዱን እንዳገኘ፣ ሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶች ያዘጋጁ እና በሜይ 1፣ 2025 ልጅዎን ያስመዝግቡ።

## My School DC ማን ያስፈልገዋል?

ልጅዎ በሚከተለው አዲስ ተማሪ እንዲሆን ከፈለጉ ማመልከቻ ያስገቡ:-

- በማንኛውም የDCPS ትምህርት ቤት የPK3 ወይም PK4 መርሃግብር (የእርስዎን የ DCPS ክልል ትምህርት ቤት ጨምሮ)
- ከወሰንዎ ውጭ የDCPS ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት ቅደም ተከተል (ከPK3-ክፍል 12)፣ በመላው ከተማ ባሉ ትምህርት ቤቶች ያሉ DCPS ጨምሮ
- በማንኛውም የDCPS የወሰን-ውስጥ ያለ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጥምር-ቋንቋ ክር (ከPK3 – ክፍል 5) ጥምር-ቋንቋ ክር
- DCPS መራጭ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም መርሃግብር (ከ9-12 ክፍሎች)
- ተሳታፊ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት (ከPK3-ክፍል 12)

ልጅዎ የሚከተሉትን ከሆነ My School DC ማመልከቻን ማስገባት አያስፈልግዎትም :-

- አሁን ባለው ትምህርት ቤቱ የሚቆይ ከሆነ (በድጋሚ ለመመዝገብ ትምህርት ቤትዎን ያግኙ)
- የነሱን የDCPS በወሰን ውስጥ ወይም በቅደም ተከተል ባለ ትምህርት ቤት ውስጥ ይመዝገቡ (ከመዋዕለ ህጻናት-12 ክፍሎች)
- በህዝብ ቻርተር ቅደም-ተከተል ትምህርት ቤታቸው ያስመዝግቡ (ሁሉም ክፍሎችን)

የMy School DC ሎተሪ ማመልከቻ በዲሴምበር 16፣ 2024 ይጀምራል። ማመልከቻው በ**እንግሊዘኛ** እና በ**ስፓኒሽ** ይኖራል። የማመልከቻ መምሪያዎች በ**አማርኛ፣ ቻይንኛ፣ ቬትናሚዝ**፣ እና **ፈረንሳይኛ** በMySchoolDC.org ላይ ለማውረድ ይገኛሉ። በቋንቋዎ የማመልከቻ እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline በ (202) 888-6336 ይደውሉ፣ ከሰኞ-አርብ፣ 8ጥዋት- 5 ከሰዓት።

**ጠቃሚ ምክር፣** በDistrict of Columbia (ኮሎምቢያ ግዛት) ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ የ K-12 ተማሪ የእኔ ትምህርት ቤት ዲሲ ማመልከቻ ሳያስገቡ በቀጥታ መመዝገብ የሚችሉበት ቢያንስ አንድ የ DCPS ትምህርት ቤት የመማር መብት አላቸው። በክልልዎ ውስጥ ያለ ትምህርት ቤት ለመፈለግ በ **MySchoolDC.org** ውስጥ ያለውን **School Finder** ይጠቀሙ።

**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

ቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline በ (202) 888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።



## የመማር ደረጃ

### መጀመሪያ፣ ለእርስዎ እና ለልጅዎ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያሰላስሉ።

- ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ስፍራ ምን ያክል አስፈላጊ ነው? ልጄን ወደ ትምህርት ቤት እንዴት አደርሳለሁ?
- የመጀመሪያ እና የመጨረሻ እንክብካቤ ለኔ ቤተሰብ ምን ያክል አስፈላጊ ነው?
- ለልጄ ምን ተመራጭ የመማሪያ ሁኔታ ምን አይነት ነው?
- ለልጄ አስፈላጊ የሆኑ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሆኑ አቅርቦቶች ምንድን ናቸው?
- ለልጄ ምን አይነት ትምህርት ነክ ያልሆኑ አቅርቦቶች አስፈላጊ ናቸው?

### ፍላጎቶችዎን የሚያሟሉ የህዝብ ትምህርት ቤት አማራጮችን በተመለከተ ይወቁ። የሚከተሉት ጥቂት ጥሩ የጅማሬ ነጥቦች ናቸው፣

- **MySchoolDC.org ይጎብኙ።**
  - በአቅራቢያዎ ያሉትን የ DCPS እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ በክልልዎ ውስጥ ያሉ የ DCPS ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በአድራሻ፣ ክፍል፣ እና በመርሃግብር አይነት ለመፈለግ **School Finder** ይጠቀሙ።
  - ስለ ተሳታፊ ትምህርት ቤቶች እና ክፍት የሆነ የቤት ውስጥ የጊዜ ሰሌዳቸውን ለማወቅ የMy School DC **የትምህርት ቤት መገለጫዎች** ይመልከቱ።
  - **የዲሲ ትምህርት ቤት የእንቅስቃሴ ካርድ** ን ይጎብኙ ተሳትፎ ያላቸው ትምህርት ቤቶች በትምህርታዊ ውጤት እና ሌሎች አስፈላጊ ነጥቦች ላይ ለማማረክ።
- ሮግራሞቻቸውን በተመለከተ ለትምህርት ቤቶች ጥያቄዎች ካሉዎት በሚችሉበት ጊዜ ትምህርት ቤቶችን ይጎብኙ ወይም በቀጥታ ለትምህርት ቤቶች ይደውሉ። ትምህርት ቤቶችን የሚጠይቋቸውን የእኛን **ጠቃሚ የጥያቄዎች** ዝርዝር ማውረድዎን እና መገምገምዎን እርግጠኛ ይሁኑ!
- እርስዎ በሚፈልጓቸው ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ ጎረቤቶችዎ ወይም ጓደኞችዎ ጋር ይነጋገሩ እንዲሁም ከትምህርት ቤት ተወካዮች ጋር ለመነጋገር እና ጥያቄዎችዎን ለመጠየቅ በዲሴምበር ወር በሚደረገው የ የዲሲ ዓመታዊ የህዝብ ትምህርት ቤት የስብሰባ ዝግጅቶች– እና በሌሎች የትምህርት ቤት ስብሰባዎች ላይ ይታደሙ።

**ምክር፦** በገጽ 1 ላይ ያለው ዎርክሺትን በመጠቀም የትምህርት ቤቶችዎን ዝርዝር ይከታተሉ!

**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

ቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline በ (202) 888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።

## የማመልከቻ ደረጃ

### መሪያ፣ የMy School DC የቤተሰብ አካውንት በ MySchoolDC.org/am ላይ ይፍጠሩ።

- አንድ የቤተሰብ አካውንት ይፍጠሩ። ይህን አካውንት ወደ አዲስ ትምህርት ቤት ለሚያመለክት ለእያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ ለማስገባት ይጠቀሙበታል። እያንዳንዱ ልጅ በቤተሰቡ አካውንት ውስጥ የራሳቸውን ማመልከቻ ያገኛሉ።
- የኢሜይል አድራሻ ማቅረብ እና የይለፍ ቃል ማዘጋጀት ይኖርብዎታል። የኢሜይል አድራሻ ከሌለዎት፣ በምትኩ የተጠቃሚ ስም መፍጠር ይችላሉ። *የመግቢያ መረጃዎን መጻፍዎን እና በአስተማማኝ ቦታ ማስቀመጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ!

### ቀጥሎ፣ My School DC ማመልከቻ ይጀምሩ።

የMy School DC ማመልከቻ ለመሙላት የሚከተሉት መረጃ ያስፈልግዎታል፣

- ስለልጅዎ መረጃ
  - ስም፣ የትውልድ ቀን፣ ያሁን ትምህርት ቤት፣ እና የሚያመለክቱበት ክፍል
  - የእህት ወይም የወንድም መረጃ
- ስለ ቤተሰብዎ መሰረታዊ መረጃ
  - የህጋዊ ሞግዚት ስም (የመጀመሪያ እና የአያት ስም)
  - የተጠሪ መረጃ፣ የሞግዚት የቤት አድራሻ ጭምር
- የትምህርት ቤት ምርጫዎች
  - እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ መምረጥ ይችላሉ
- የትምህርት ቤት ደረጃ አወጣጥ
  - 1ኛ ምርጫዎን (በጣም የሚፈልጉትን ትምህርት ቤት)፣ ከዚያ 2ኛ ምርጫ፣ እና ወዘተ እያሉ ይዘርዝሩ። ምርጫዎችዎ እርስዎ በጣም በሚወዱት ቅደም ተከተል ደረጃ እንደተሰጣቸው ለማረጋገጥ ምርጫዎችዎን በድጋ

**አስፈላጊ፦** ለእርስዎን ትምህርት ቤቶች የሰጡት ደረጃ ቅደም ተከተል ወሳኝ ነው! ሎተሪው ሁሉም አመልካቾች በዋናነት ደረጃ ከሰጡት(#1) ትምህርት ቤት ጋር ለማዛመድ ይሞክራል። ተማሪዎች መዛመድ የሚችሉት እስከ አንድ ትምህርት ቤት ብቻ ሲሆን ከተዛመዱበት ወይም ከተመዘገቡበት ትምህርት ቤት በላይ ደረጃ በሰጧቸው ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ።

### በመጨረሻ፣ ማመልከቻዎን በመጨረሻ የጊዜ ገደብ ያስገቡ!

- ፌብሪዋሪ 3፣ 2025፦ ከ9-12ኛ ክፍል ላሉ የማመልከቻ ቀነ ገደብ
- ማርች 3፣ 2025፦ ከPK3 –8ኛ ክፍል ላሉ የማመልከቻ ቀነ ገደብ

ማስታወሻ፦ በማመልከቻዎ ላይ ማንኛውም ማሻሻያዎች ለማድረግ እስከ ጊዜ ገደቡ የመጨረሻ ቀን ድረስ እና ከፈለጉ የትምህርት ቤት ደረጃ ዎችዎን በድጋሚ ለማዘዝ እስከ ማርች 14 ድረስ ጊዜ አሎት።

**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline በ (202) 888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።

**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

ቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline በ (202) 888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።



## የመመዝገቢያ ደረጃ

### የሎተሪ ውጤቶችዎን ሲቀበሉ ምን ማድረግ አለብዎ?

የሎተሪ ውጤቶች በ **ማርች 28፣ 2025** ላይ ይገለጻሉ። የልጅዎን በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ያለውን ቦታ በ **MySchoolDC.org** የቤተሰብዎ መለያ ውስጥ ይግቡ።

ልጅዎ ከትምህርት ቤት ጋር በሎተሪ ከተዛመደ፣ በዚያ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ እስከ **ሜይ 1፣ 2025**። ጊዜ አሎት። ልጅዎ ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ቦታ ከተሰጠው፣ በትምህርት ቤቱ በተነገርዎት የመጨረሻ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስመዝገብ አለብዎት። በእነዚህ የመጨረሻ የጊዜ ገደቦች የማያስመዘግቡ ቤተሰቦች በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቦታቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ ልጃቸውን ለማስመዝገብ የትምህርት ቤቱን ምዝገባ እና የመኖሪያ ፈቃድ ማረጋገጫ ሂደቶች ማጠናቀቅ አለባቸው።

ለመመዝገብ፣ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦

- የDC ነዋሪ መሆንዎን ማረጋገጥ። የቤትዎን አድራሻ ለማሳየት ሊጠቀሟቸው የሚችሉ የሰነዶችን ዝርዝር ለማየት ወደ OSSE.dc.gov ይሂዱ።
- ሁሉንም ማስገባት የሚያስፈልገውን የጤና እና የክትባት መዝገቦችን ጨምሮ፣ የትምህርት ቤቱን ተጨማሪ የመመዝገቢያ መስፈርቶች ይከተሉ።

**በተዛመዱበት ትምህርት ቤት ልጅዎን ማስመዝገብ ልጅዎን ከሌሎች ትምህርት ቤቶች የተጠባባቂ ዝርዝር እንዲሰረዝ**

**አያደርገውም።** የልጅዎ በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ አሁን ያለውን ቦታ በማናቸውም ጊዜ በ **MySchoolDC.org** የቤተሰብዎ አካውንት ውስጥ በመግባት ማየት ይችላሉ። ከተጠባባቂ ዝርዝር የሚገኙ አቅርቦቶች ዋስትና የላቸውም።

የእርስዎን የዕጣ ውጤቶች መረዳትን በሚመለከት እና ተጠባባቂ ዝርዝሮች እንዴት እንደሚሰሩ መረጃ ለማግኘት ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።



**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

ቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline በ (202) 888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።

# ማስታወሻዎች

# MY SCHOOL DC
## የህዝብ ትምህርት ቤት ሎተሪ

MY SCHOOL DC
የሕዝብ ት/ቤት ሎተሪ

**የቁልፍ ቀናት**

**ዲሴምበር 7፣ 2024 | EdFEST (**ከ **9-12**ኛ ክፍሎች**)**
**ዲሴምበር 14፣ 2024 | EdFEST (**ከ**PK3 – 8**ኛ ክፍል**)**
**ዲሴምበር 16፣ 2024 |** የ**My School DC** ማመልከቻ ይከፈታል
**ፌብሪዋሪ 3፣ 2025 |** ከ **9-12**ኛ ክፍሎች የማመልከቻ ቀነ ገደብ
**ማርች 3፣ 2025 |** ከ **PK3 – 8**ኛ ክፍል የማመልከቻ ቀነ ገደብ
**ማርች 28፣ 2025 |** የእጣ ውጤቶች ይለቀቃሉ
**ኤፕሪል 26፣ 2025 |** ምዝገባ ቀዳሜ
**ሜይ 1፣ 2025 |** ለተዛመዱ ተማሪዎች የምዝገባ ቀነ ገደብ

For assistance in your language, call **(202) 888-6336.**
Para recibir ayuda en su idioma, llame al **(202) 888-6336.**
በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት፣ ይደውሉ **(202) 888-6336**።
如果需要语言方面的帮助，请拨打 **(202) 888-6336**。
Để được hỗ trợ bằng ngôn ngữ của quý vị, hãy gọi **(202) 888-6336**.
Pour obtenir de l’aide dans votre langue, appelez le **(202) 888-6336**.

**/MySchoolDC**
**MySchoolDC**
**@MySchoolDC**
**@MySchoolDC**


**www.myschooldc.org/am**
**(202) 888-6336**
**info.myschooldc@dc.gov**



OSSE
WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR